የጎንደር ሕብረት

gonderhibrert72@gmail.com /website: www.gonderhibret.org

# “ቃል ይተከላል፤ ቃል ይነቅላል”

## ዶ/ር አብይ አህመድ

በብዙ አገር ወዳድ ጀግኖቻችን ደም ታጥባ፤ በአጥንታቸው ታጥራ፤ በእስትንፋሳቸው የእሳት ወላፈን እንደ ወርቅ ተነጥራ የተሰራች አገራችን ኢትዮጵያ ከሁለት አሥርተ ዓመታት በላይ ከባድ ፈተና ቢያጋጥማትም፤ ዛሬም እንዳለፉት ጀግኖች ልጆቿ በፈተና ጸንታ ለእንበለ ጽድቅ እንደምትበቃ አንዳችም ቀን ተጠራጥረን አናውቅም ነበር።

“የቸኮለ ጅብ ቀንድ ይነክሳል” ሊያስተርት ይችል ይሆናል። ነገር ግን ኢትዮጵያ አገራችን ከሃያ ሰባት ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በምኒልክ ቤተ መንግሥት ውስጥ በገቡ መሪዎቿ ስሟ ነግሶ የዋለበት፤ በዘመናት ሁሉ የተሰሩት ታሪኮቿ ለአንድ ጎሳ ወይም አካባቢ ሳይወሰን በሁሉም ልጆቿ ደም ተለውሳ የተሰራች የሁላችን አገር መሆኗ፤ ማንም ከማንም በላይ የወርቅ ዘር እንዳልሆነ፤ ይልቁንም የብዙዎቻችን ድምር ውጤ እንደሆነች ሲመሰከርላት ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑ በማየታችን፤ ዛሬን አድንቀን የነገውን የቤት ሥራችን ሁላችንም በዘመናዊ የሂሳብ ሥሌት ሳንታገዝ ተፈጥሮ በአደለን እዕምሮ፤ ብስለት በተሞላበት ጭንቅላታችን ተገዝተን አገራችን የምትጠይቀውን የዜግነት ግዴታ እንድንወጣ ታላቅ ሸክም ተጥሎብናል።

ዶ/ር አብይ ለቤተ መንግሥት መጀመሪያ ቀን በሆነው የማህላ ሥነ ሥራዓት ንግግራቸው ከሚወዷት ኢትዮጵያ አገራቸው ተነሥተው፤ እናታቸውን፤ ውዷ ባለቤታቸውን፤ ጓደኞቻቸውን፤ ለወደፊት ሊሰሩ ያቀዱትን፤ በአጠቃላይ የገቡትን ቃል ኪዳናቸውን አነሳስተን የተጠቀሙበትን አምላካዊ ቃል ደማምረን ድንቅ የቃላት አጠቃቀማቸውን ሁሉ ሥንተርክ ብንውል ብናድር በአንድ መግለጫ ቀርቶ በመጽሐፍ አንጠቀልለውም። በጥቅሉ ኢትዮጵያን ለሚወድ ዜጋ ሁሉ የሚማርክ ነበር። ይሁን እንጅ፤ ዶ/ር አብይ ከተናገሩት ብዙ ቁም ነገሮች ለዛሬ መጣጥፋችን አንዷን ብቻ መዘን ትዝብቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ፤ መልሱን ከሳቸው እንጠብቅ። ዛሬ ምኒሊክ ቤተ መንግሥት እንደሚገቡ ራዕይ የነበራቸው እናታቸው በትጋትና በእንክብካቤ አሳድገዋቸው ለዚህ መብቃታቸውን በመላ ኢትዮጵያ ፊት ቆመው መሰከሩ፤ አመሰገኑ!

ታድያ! ዛሬ የተረከቧት ኢትዮጵያ በሺዎች የሚቆጠሩ እናቶች ይህን አይነት እድል ለማየት ውኃና እንጨት በጭንቅላታቸው ተሸክመው፤ ማንኛውንም ዓይነት ሳንቲም የሚያወጡ ጥቃቅን የሽያጭ ሸቀጦችን በመሸጥ በቀን አንዴ በልተው አንጀታቸው በርሃብ እንደታሰረ ሁለተኛውንና ሶስተኛውን ማእዳቸውን ቀን ያወጣልኛል ለሚሉት ልጃቸው አጉርሰው በተስፋ ያሳደጓቸው ለቁምነገር ይደርሳሉ ተብለው የሚጠበቁ ፤ የተስፋ ዓይንን የሞሉ ልጆቻቸው በአረመኔው የአጋዚ ጥይት በጭካኔ እየተረፈረፉ ነው ያሉት። በሺ የሚቆጠሩ እድሜ ለይተን የማንዘረዝራቸው ንጹኃን ዜጎች የሰባዊ መብትና የዴሞክራሲ ጥያቄ በመጠየቃቸው ብቻ ተወንጅለው በየእስር ቤቱ ያለ ፍርድ ረዥም ወራትንና ዓመታትን አስቆጥረዋል። ከዚህስ በኋላ ይህ ታላቅ የህሊና ሸክም፤ የብዙ እናቶች ልብ ለአንዴም ለመጨረሻም ከኃዘን ስብራት የሚጠግንበት፤ ነገም ሌሎች እናቶች የኃዘን ልብስ ከመልበስ የሚታደጋቸው ፍርኃተ እግዚአብሔር ያለው ዜጎቹን አክባሪ አገሩን መሪ ይሆናል ብለው እንዲያምኑ የዶ/ር አብይ ቃል እውን ሊሆን ይሆን?

ዶ/ር አብይ የገቡት ቃል በውስጣቸው ይዘው በተንሱት የግል ወኔ ሊሆን እንደሚችል ብንገምትም፤ እርሳቸው ቃል እንደገቡት፤ ብዙዎችም እንደሚያስቡት መንገዱ አልጋ ባልጋ አይደለም። እጅግም ጠማማው መንገድ ለ27 ዓመት በሰይጣኖች የዘር ድግምት የተተበተበ የቢሮክርሲ አምባሳደሮች ወይም ሆዳም ጉቦኞች በየመዋቅሩ ተሰግሥገው የዜጎችን ብቻ ሳይሆን

አንጡራ ኃብታችንን እያሚጠጡ ከአገር ውስጥ እስከ ውጭ በማጓጓዝ አገራችንን ባዶዋን ያስቀሩትን ጭምር ነው ሊያፀዱ የተረከቡት።

በመሆኑም በጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት እምነት፤ ከላይ የጠቀስናቸውም ሆነ ለኢትዮጵያ አንድነት አደጋ የሆነውን ህገ መንግሥቱን ጨምሮ የተለያዩ የአገራችን ችግሮች በአንድ ሰው ቸርነትና ትጋት እንዲያውም ለ27 ዓመት የኢትዮጵያን ሕዝብ በወሬ ብቻ እያደናቆረ ውጥንቅጧን አውጥቶ በተጠላ ፓርቲ (ኢህአዴግ) ውስጥ ከወጣ መሪ  ሙሉ በሙሉ ለውጥ ይመጣል ተብሎ ጭራሹን አይታሰብም። ምክንያቱም ከዶ/ር አብይ ጀርባ ሸር የሚጠመጥሙ የአገር ጠላቶች ተሰግስገዋል እና። ስለዚህም ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር ጠቅላይ ሚኒስተር ኃይለማርያም ደሳለኝ አልነበሩም የምንለው። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለረዥም ዘመናት የሚፈልገውን ለውጥ ለማምጣት በትግሥት የተለያዩ አጋጣሚዎችን ተጠቅሞ ታግሎ ይህ ሥራዓት እስካለ ድርስ ፈጽሞ ሰላማዊ በሆነ መልኩ ፍትሕና ዲሞክራሲዊ እኩልነት የሰፈነበት ኢትዮጵያን ማየት እንደማይቻል አውቆ የሥር ነቀል ለውጥን አንግቦ የሞት የሽረት ትግል እያደረገ ባለበት ወቅት ላይ ነው ዶ/ር አብይ ወደ ሥልጣን የመጡት።

ዛሬ ዶ/ር አብይ የገቡት ቃል እንዲተከልላቸው እሳቸውንም እንዳይነቅላቸው ከፈለጉ የሚከተሉትን ተግባሮች በአስቸኳይ ፈጽመው ከኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ይጎዘጎዙ። እኛም ከጎናቸው ቆመን ለዚያች አገር ታሪክ  የበኩላችን እንሥራ፡-

1. መብታቸውንና ማንነታቸው እንዲከበርላቸው በመጠየቃቸው ብቻ እንደ አሸባሪ ተቆጥረው ለረዥም ጊዜ በየእሥር ቤቱ እንደ ሰርዲን የታጨቁትን፤ ጨለማ ቤት የተዘጉትን የሞራል ካሳ በመክፈል በአስቸኳይ ይፍቱ፤ ድጋሚም በፖለቲካ  እይታቸው ምክንያት ዜጎች ወደ እስር ቤት የማይወረወሩ መሆናቸውን ያረጋግጡ።
2. ዜጎችን እጅ ከወርች አስሮ የያዘውን የማፈኛ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በአስቸኳይ ያንሱ።
3. ይህ አሁን እሰራበታለሁ የሚሉት ሥራዓት በሁሉም ኢትዮጵያውያን ያሰራል ተብሎ ስለማይታመንበት፤ በአስቸኳይ ሁሉን አቀፍ ብሔራዊ እርቅ የሚጠራበትን መድረክ ፈጥረው፤ የሽሽግግር መንግሥት የሚዋቀርበትን ሁኔታ ያመቻቹ።
4. በቃልዎ መሰረት “ተፎካካሪ” ብለው በአማረ ቋንቋ ያስጌጧቸውን በተለያየ አመለካከት የተደራጁ ድርጅቶች ለደህንነታቸው ዋስትና ያለው አዋጅ በማወጅ በሰላም ወደ አገራቸው ገብተው ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ያላቸውን ራእይ  የሚሸጡበትን መድረክ ያዘጋጁ ዘንድ እንጠይቃለን።

ውድ የጎንደር/ኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሁም በተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች በቄሮ፤ በፋኖ፤ በዘርማ ስም የተደራጃችሁ ፋና ወጊ የነፃነት ታጋዮች ሆይ! ባለፉት 27 ዓመታት የተወጠረው እንዲላላ ጨልሌው የወያኔ መንግሥት የተለያዩ ተስፋዎችን ሲያሳይህ ቆይቷል። በእርግጥ በአሁኑ ሰዓት በምኒልክ ቤተ መንግሥት የተፈጠረው ሁኔታና የዶ/ር አብይ መምጣት የተለያ ቢያደርገውም፤ ዶ/ር አብይ ይዘው የተነሱትን ቀናኢ ራዕይ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ትግልክን የበለጠ አጠናክረህ ቀጥል። ከእሳቸው ጎን እንደምትቆምም በመላ አገሪቱ ሰላማዊ ሰልፎችን በመጥራት የድጋፍ ድምፅህን አሰማ።

የጎንደር ሕብረት

gonderhibrert72@gmail.com /website: www.gonderhibret.org

በጎንደር ሁመራ እስከ ጋምቤላ ያለው የአገራችን ዳር ድምበር መከበሩ ገና አልተረጋገጠም። ወያኔ የመሬት ጥሙን ለማርካት ተከዜን ተሻግሮ በጎንድርር ክ/ሀገር ንጹሃን የወልቃይት ሁመራ፤ የጠገዴና የፀለምት ወገኖቻችንን እክስካሁንም እየጨፈጨፈ ብዙዎችን አፍሶ ትግራ ድረስ በመውሰድ በእስር ቤት እያሰቃየ ያለበት ወቅት ላይ ነንን። ጎንደርን በጎሳ ፖለቲካ ለማመስ ያወጣውን እቅዱንም አልተወውም። ያዝ ለቀቅ እያረገ ህዝባችን ለማዘናጋት እያደባ ነው ያለው።

በአጠቃላይ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን በእየ እሥር ቤቱ ያለ ሃጥያታቸው የመሬትን ፍዳ እየከፈሉ፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአስቸኳይ አዋጅ እጅት ተወርች ተቀፍድዶ በሚገኙበት ወቅት፤ የኢትዮጵያ አደጋ በሆነው ህገ መንግሥት ውስጥ ነጥረው የዘለቁትን ዶ/ር አብይን ብቻቸውን ለውጥ ያመጣሉ የሚል ተስፋን ሰንቀን ፈጽሞ ከትግል ልንዘናጋ አይገባንም። ሁሉም የምንፈልጋቸው የመብት ጥያቄዎቻችን እስኪሟሉ ትግላችን ይቀጥላል።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

የጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት።

04-03-2018